
Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# ስለ 2020 ፎል የ MCPS የመንሠራሪያ-ማገገሚያ እቅድ እሳቤዎች

MCPS ፎል 2020፡-እንደገና ስለመክፈት፣ መንሠራራት ማገገም ማሰብ



# ማውጫ


የሱፐርኢንተንደንት ደብዳቤ ...3

ትምህርት ቤቶችን ስለመከፈት የስቴት መስፈርቶች ...4

የእኛ መርሖች ...5

ስለ ተማሪዎች መመለስ ...6

ስለ ቅይጥ ቨርቹወል ትምህርት -ሞዴል 1...7

ቨርቹወል ቅይጥ የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ናሙና መርሃግብር ...8

ቨርቹወል የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናሙና መርሃግብር ...9

ቨርቹወል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናሙና መርሃግብር ...10

ቨርቹወል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናሙና መርሃግብር (የቀጠለ) ...11

ቨርቹወል ትምህርት ብቻ - ሞዴል 2 ...12

የኤለመንተሪ ቨርቹወል ትምህርት ብቻ ናሙና መርሃግብር ...13

የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቨርቹወል ትምህርት ብቻ ናሙና መርሃግብር ..14

የመተግበር ትልሞች ...15

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ወደ ቤት በሠላም ማጓጓዝ ...15

ጠንካራ የጤንነት እና የደህንነት ጥንቃቄዎች ...16

የምግብ አገልግሎቶች ...17

የማገገሚያ እቅድ የጊዜ ማዕቀፍ ...18

በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች ...19

ግብረመልስዎን ያቅርቡ ...20

# የሱፐርኢንተንደንት ደብዳቤ

**የተከበራችሁ ወላጆች፣ ሞግዚቶች፣ ሠራተኞች እና ተማሪዎች**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ 2020-2021 የትምህርት ዓመት ስለሚጀመርበት እቅድ እና ዝግጅት ባለፉት በርካታ ወራት በትጋት ሲሠራ ቆይቷል። የ 2019-2020 የትምህርት ዓመትን 75 በመቶ በሥራ እና በማስተማሪያ ክፍሎች፣ በትምህርት ቤቶች እና በጽ/ቤቶች በትብብር ለማጠናቀቅ ችለናል። ነገር ግን ከማርች 16፣ ጀምሮ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ህንፃዎች መምጣት እንዲያቆሙ ስለተደረገ እና—ሁላችንም በስጋት—ጁን 15 የትምህርት ዓመቱ እስከሚጠናቀቅበት ቀን አልተመለስንም። አሁን፣ እንደገና መሰናዶ በማድረግ እና ስለ 2020-2021 የትምህርት ዓመት በማሰብና በዝግጅት ላይ ተጠምደናል።

እናንተም ለመገመት እንደምትችሉት ሁሉ፣ ይህ ሥራ እጅግ በጣም አዳጋች እና ከፍተኛ ውስብስብነት አለው። ትምህርት ቤቶችን ዳግም ስለ መክፈት በርካታ የተለያዩ ሞዴሎችን ተወያይተናል እና ገምግመናል፣ እና እንደእውነቱ ከሆነ፣ የእኛ የትምህርት ሲስተም ያጋጠመውን የማስተማሩን፣ የሥራ ሂደትን እና የአቅርቦቶችን ውጣ ውረዶች በሙሉ ለማሟላት የሚያስችል አንድ ብቸኛ አማራጭ የለም። በስፐሪንግ ወቅት የትምህርት ቤቶች ሳይታሰብ በድንገት መዘጋት እና ስለ ፎል እርግጠኛ መሆን አለመቻል በቤተሰቦች ላይ ከፍተኛ መጨናነፍ እና ውጥረት መፍጠሩን እንገነዘባለን። ቤተሰቦች ከሁኔታቸው በመነሣት የገለጹልንን ገጠመኞቻቸውን እና ፍላጎታቸውን በርካታ አተያይ ግምት ውስጥ አስገብተናል። ከሁሉም በላይ፣ እኛ ያቀረብናቸው አማራጮች በሙሉ በፍትሃዊነት እና በሚዛናዊነት፣ እንዲሁም በከፍተኛ ጥራት-ምጡቅነት፣ መነጽር መታየት ያለባቸው ሲሆን የ 166,000 ተማሪዎችን እና የ24,000 የሥራ ባልደረቦችን ጤንነት እና ሠላም በሚያረጋግጥ ሁኔታ መሆን አለበት።

ስለ ማስተማር እና መማር ድጋሚ መሰናዶ ማድረግ እና እንደገና መተለም የ MCPS ተማሪዎችን ጥራት ያለው ትምህርት-ምጡቅነትን ላለማሳካት እና ፍትኃዊነትና ሚዛናዊነት ለማዳበር እንቅፋት ሊሆን ወይም ምክንያት ሊሆን አይችልም። ተማሪዎቻችን በእኛ ይመካሉ። እኛ ተስፋ ያደረግነው ወይም እንደገመትነው ባይሆንም እንኳ፣ ባልተጠበቀ መንገድ—አዲስ የጤና መመሪያዎችን-ፕሮቶኮሎችን፣ አካላዊ ርቀት መጠበቅን እና ሌሎች በርካታ ነገሮችን ጨምሮ የ 2020-21 የትምህርት ዓመትን እንጀምራለን።

ለፎል የእኛን አንዳንድ የመነሻ እሳቤዎች እና እቅዶቻችንን ለእናንተ ለማጋራት ደስታ ይሰማኛል። የ MCPS Fall 2020፡- ዳግም መተለም፣ ዳግመኛ መከፈት፣ ማገገም-ወደ መደበኛ ሁኔታ የመመለስ መመሪያ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት እና ከካውንቲአችን የጤና አጋሮች ባገኘነው መረጃ እና መመሪያ መሠረት በዚህ ወቅት የምናስባቸውን ጥቂት የማገገሚያ ሞዴሎችን አጠቃላይ እይታ ግንዛቤ ይሰጣል። ይሄ ***ረቂቅ መመሪያ መሆኑን*** በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ እና ከእናንተ—ከአጋሮቻችን፣ ከሠራተኞች እና ከተማሪዎች ምክረሃሳቦችንና ግብረመልሶችን ካገኘን በኋላ በእነዚህ አስተያየቶች ላይ ማሻሻያዎችን፣ ማስተካከያዎችን ማድረግ እንቀጥላለን። እነዚህን ረቂቅ አማራጮች በምታዩበት ጊዜ በርካታ ጥያቄዎች እና አሳሳቢ ነገሮች ሊኖራችሁ እንደሚችል እናውቃለን። በመጪዎቹ ሣምንታት እናንተን የሚያሳስቧችሁን ነገሮች እና ጥያቄዎቻችሁን ምላሽ ለመስጠት እያንዳንዱን እርምጃ ከእናንተ ጋር እንደምንሠራ ልናረጋግጥላችሁ እንፈልጋለን።

እነዚህ እሳቤዎች ተማሪዎች በአካል ተገኝተው ለመማር እና MCPS ለተማሪዎቻችን በማዘጋጀት ላይ ያሉ የተለያዩ የማስተማር አማራጮችን እና ወደ ትምህርት ቤት በሚመለሱበት ወቅት ተግባራዊ ስለሚደረጉ የጤንነትና ደህንነት መመሪያዎችና-ፕሮቶኮሎች አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣሉ። ለእሳቤዎቹ መንስዔ የሆኑት አሁን ያለውን ዳታ-መረጃ መሠረት በማድረግ የቀጠለው አጠቃላይ የጤና አቅጣጫን መሠረት ያደረጉ ናቸው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎቻችን ወደ ትምህርት ቤት ህንፃዎች እንደሚመለሱ እና የኮቪድ-19 ተፅእኖን በመቀነስ ረገድ ቁርጠኛ ነው። ነገር ግን፣ ወረርሽኙ የሚከሰትበትን መንገድ አስቀድመን ለመተንበይ ባለመቻላችን ምክንያት—አሁን ያሉት ሁኔታዎች ከተለወጡ—የተማሪዎቻችን እና የሠራተኞቻችን ሠላምና ደህንነት ግንባር ቀደም የእቅዳችን አካል ስለሚሆን MCPS እነዚህን ትልሞች እንደገና ይመለከታል።

ለእያንዳንዱ ተማሪ ትምህርት ለማስተማር እና እድሎችን ለመፍጠር አጽንኦት ለመስጠት ሃላፊነት እንወስዳለን። የቤተሰቦችን፣ የተማሪዎቻችንን እና የሠራተኞቻችንን ፍላጎት በማሟላት ረገድ በጋራ አጠቃላይ እቅድ ለመገንባት በቀጣይነት ስለሚያደርጉልን ትብብር እና ድጋፍ አመሰግናለሁ።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

Jack R. Smith
Superintendent of Schools

# ሪሶርሶች እና መስፈርቶች

የማገገሚያ እቅድ ስለማዘጋጀት

## ትምህርት ቤቶችን ስለመክፈት የስቴት መስፈርቶች

### የትምህርት ዲስትሪክቶች ማድረግ ያለባቸው፦

- የማገገሚያ እቅዶችን አጠናቀው ኦገስት 14 በዲስትሪክት ድረ-ገጽ ላይ ማውጣት አለባቸው። እቅዶቹን በሙሉ የስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ይገመግማቸዋል።
- በሁሉም የእቅዱ ክፍል ላይ ስለ ፍትሃዊነት እና ሚዛናዊነት ትኩረት መስጠት አለበት።
- ትምህርት ቤታቸውን እና ማህበረሰባቸውን የሚወክሉ የማገገሚያ እቅድ ባለድርሻ አካላት ቡድን ያቋቁማሉ።
- በትምህርት መካከል ያለውን ክፍተት ለይቶ ለማወቅ ሁሉንም ተማሪዎች ይመዝናሉ/ይገመግማሉ።
- የ MSDE መስፈርቶችን በመከተል በሁሉም ቁልፍ ነገሮች ዙርያ መመሪያ/ግንዛቤ ይሰጣሉ።
- IDEA፣ 504 እና ADA በተጨማሪም ሌሎች የስፔሻል ኢጁኬሽን ፕሮቶኮሎችን እና ህጎችን ይከተላሉ።
- ኮቪድ-19 ለተገኘባቸው ግለሰቦች የ MSDE፣ የስቴት እና የፌደራል የጤና መመሪያ እና አሰራሮችን ይከተላሉ።
- ስለ ምግብ አገልግሎቶች፣ የእለት ተእለት ጽዳትና ንጽሕና እንዲሁም ሌሎች አሠራሮችን በሚመለከት የ MSDE፣ የስቴት እና የፌደራል የጤና ፕሮቶኮሎችን ይከተላሉ።
- ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ወደቤት ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የማጓጓዝ ፕሮቶኮሎችን ይከተላሉ።
- ተማሪዎች በርቀት ትምህርት ላይ በሚሳተፉበት ወቅት ክትትል እንደሚያደርጉ የማረጋገጫ ስልት ያዘጋጃሉ።
- የባለድርሻ አካላትን የሚያገኙበት የመገናኛ ዘዴ እቅድ ያዘጋጃሉ/ይኖራቸዋል።

### መገልገያዎች/ሪሶርሶች

- ሜሪላንድ በአንድነትና በአብሮነት፡- የሜሪላንድ ወደ ጤናማ ሁኔታ የመመለስ-ማገገሚያ የትምህርት እቅድ
- ለሠራተኞች እና ለቤተሰቦች የ 2020 ሠመር ፕሮግራሞች ዳሰሳ
- ለሠራተኞች እና ለቤተሰቦች የ 2020 ፎል ወደ ጤናማ ሁኔታ የመመለስ ዳሰሳ
- በስቴት እና በአገሪቱ ከፍተኛውን የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ጋር ጥራትን በማነፃፀር ማመዛዘን

# የእኛ መርኆዎች

ትምህርት ቤቶችን ዳግም ስለመክፈት

- የተማሪዎችን እና የሠራተኞችን ደህንነታቸውን ማረጋገጥ
- የትምህርት አሠጣጥ ዘይቤው-ሞዴል የፈለገም ቢሆን ለተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ማስጠት
- ሁሉም ማለት ሁሉንም የሚመለከት መሆኑን በፍትኃዊነትና በሚዛናዊነት ማረጋገጥ
- ሪሶርሶችን በአግባቡ መጠቀም (ቦታዎችን እና ቁሳቁሶችን)
- በእቅድ ዝግጅት ላይ የማህበረሰብ እና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማረጋገጥ

# የተማሪዎች መመለስ

ለሁሉም ተማሪዎች የ 2020-2021 የትምህርት ዓመት ሰኞ፣ ኦገስት 31/2020 ይጀመራል። በትምህርት ቤት ህንፃ ውስጥ በአነስተኛ የመማሪያ ክፍሎች እና በአነስተኛ የተማሪዎች ቁጥር በአካል ተገኝተው ለመማር ተማሪዎች በፈረቃ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሣሉ። በአቅም ውስንነት ምክንያት፣ የማጓጓዣ መገልገያዎች ለኤለመንተሪ እና ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቅድሚያ ይሰጣል። ግባችን እስከ ታንክስጊቪንግ-Thanksgiving በሁሉም የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በፈረቃ በትምህርት ቤት እንዲሆኑ ነው። በትምህርት ዓመቱ የመጀመሪያ ወሮች ላይ ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው፣ በአያት ስማቸው (last name) ቅደምትከተል እና በክለስተር ቀስበቀስ-በየደረጃው-in phases ወደ መማሪያ ክፍሎቻቸው ይመለሳሉ።

## የትግበራ መርኃግብር

- የወቅቱን የህዝብ ጤንነት ሁኔታ፣ የቤተሰቦቻችን ፍላጎት እና ለሠራተኞች እና ለተማሪዎቻችን ስለ ኮቪድ-19 በቂ ስልጠና መስጠትን ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ዓመቱን በርቀት ትምህርት ሞዴል ብቻ ለመጀመር ይታሰባል።
- በትምህርት ቤቱ ደረጃ እና ክፍል/እድሜ ተመስርቶ የቀስበቀስ-በየደረጃው-in phases ከ2 - 4 ሣምንቶችን ይወስዳል.
- የቀስበቀስ-በየደረጃው-in phases አሠራር የህዝብ የጤንነት ሁኔታዎች ላይ የሚታየውን መሻሻልና የትግበራ ተሞክሮዎችን ተከትሎ ይስተካከላል.
- ዝርዝሮቹ እና ቀኖቹ ይቀጥላሉ።

## Sequencing/ቅደም-ተከተል ማስያዝ

በተለይ የስፔሻል ኢጁኬሽን ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት አዲስ የሆኑ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች (ቅድመ ምዋእለ ህፃናት፣ ምዋእለ ህፃናት፣ 6ኛ እና 9ኛ ክፍሎች) ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የመጀመሪያዎቹ ይሆናሉ።

### ኤለመንተሪ ት/ቤት

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያ ደረጃ-Phase 1 | ቅድመ ምዋእለ ህፃናት፣ ምዋእለ ህፃናት እና በተለይ በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች |
| ሁለተኛ ደረጃ Phase 2 | ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ክፍሎች Grades 1 - 2 |
| ሦስተኛ ደረጃ-Phase 3 | ከ3ኛ እስከ 5ኛ ክፍሎች |

### መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Middle School)

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያ ደረጃ-Phase 1 | ስድስተኛ ክፍል-Grade 6፣ በተለየ ስፔሻል ኢጁኬሽን ፕሮግራሞች የሚገኙ ተማሪዎች |
| ሁለተኛ ደረጃ-Phase 2 | 7ኛ ክፍል |
| ሦስተኛ ደረጃ-Phase 3 | 8ኛ ክፍል |

### ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (High School)

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያ ደረጃ-Phase 1 | ዘጠነኛ ክፍል-Grade 9፣ በተለየ ስፔሻል ኢጁኬሽን ፕሮግራሞች የሚገኙ ተማሪዎች |
| ሁለተኛ ደረጃ-Phase 2 | 10ኛ ክፍል |
| ሦስተኛ ደረጃ-Phase 3 | ከ 11ኛ - 12ኛ ክፍሎች |

# ቅይጥ- የቨርቹወል ትምህርት—ሞዴል **Blended** Virtual Learning—Model 1

## የማስተማር እሳቤዎች

- እኛ ግባችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በሙሉ በአካልም ሆነ በርቀት ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ተሞክሮዎችን መስጠት ነው።
- በቨርቹወል ትምህርት ላይ ያተኮረ እና የተቻለውን ያክል በርካታ ተማሪዎችን በአካል ተከታታይ እና በፈረቃ ትምህርት የመስጠት **እቅዶችን በከፍተኛ ጥረት እየሠራን ነው።**

## ወቅታዊ ምክረ ሃሳቦች

### ቅይጥ ቨርቹወል ትምህርት

- መርኃግብሩ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የህዝብ የጤንነት ሁኔታዎችን እና የትግበራ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ ለውጥ የሚደረግበት ይሆናል።
- የማጠቃለያ መርሃግብሩ እና ድጋሚ የመክፈት እቅዱ ሲገለጽ ቤተሰቦች ቨርቹወል ትምህርት ብቻ የመምረጥ አማራጭ አላቸው።

ለኤለመንተሪ እና ለመካከለኛ ትምህርት ቤት በፈረቃ A/B መርሃግብር በክፍል ደረጃ፣ በተማሪ የመጨረሻ ስም/የቤት አድራሻ፣ እና በትምህርት ቤት ክለስተር።

| ሰኞ & ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ & ዓርብ |
|---|---|---|
| ቡድን A በትምህርት ቤት<br><br>ቡድን B እቤት በቨርቹወል ትምህርት | ሁሉም ተማሪዎች እቤት ቨርቹወል ትምህርት<br><br>ለሠራተኞች የሙያ ማዳበር | ቡድን B በትምህርት ቤት<br><br>ቡድን A እቤት በርቀት ትምህርት |

* የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እየጨመረ እንዲዘጋ ሁኔታው የሚያስገድድ ከሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በስቴት እና/ወይም በአካባቢ ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ሁሉንም ተማሪዎች ወደ ቨርቹወል ትምህርት ብቻ ለመመለስ ይዘጋጃል።

# ቅይጥ የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት የቨርቹወል ትምህርት ሞዴል መርሃግብር

(ቅይጥ ቨርቹወል ትምህርት ማለት በአካልና በቨርቹወል በሁለቱም ተደባልቆ የሚሰጥ ትምህርት ነው)

| | ቡድን A ሰኞ እና ማክሰኞ | ረቡዕ | ቡድን B ሐሙስ እና ዓርብ |
|---|---|---|---|
| A.M. | መድረሻ/ቁርስ | • ተማሪዎች ሳይጠጋጉ ተራርቀው መማር እና በተናጠል መሥራት *<br>• ለሠራተኞች የተናጠል እና በትብብር የመሥራት እቅድ<br>• ስለ ማርክ አሠጣጥ<br>• የሙያ እድገት<br>• በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ | መድረሻ/ቁርስ |
| | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ | | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ |
| | ስነጥበብ_ሙዚቃ_የአካል ማጎልመሻ ትምህርት Art/Music/P.E. | | ስነጥበብ_ሙዚቃ_የአካል ማጎልመሻ ትምህርት Art/Music/P.E. |
| | ምሳ | | ምሳ |
| | እረፍት _ ለ "classes of 15" ክፍሎች ቀኑን ሙሉ ውጭ እረፍት ላይ የሚሆኑበት የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል<br>የተደራሽነት ገደብ ያለባቸው አካባቢዎች<br>በፈረቃ የመምህር እቅድ | * ማሳሰቢያ:- የ A/B ቡድን ፈረቃ፣ በእሮብ ቀኖች የቀጥታ ስርጭት ትምህርት አይኖርም | እረፍት _ ለ "classes of 15" ክፍሎች ቀኑን ሙሉ ውጭ እረፍት ላይ የሚሆኑበት የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል<br>የተደራሽነት ገደብ ያለባቸው አካባቢዎች<br>በፈረቃ የመምህር እቅድ |
| ከሠዓት በኋላ_P.M. | ሂሳብ | | ሂሳብ |
| | ሳይንስ/ማህበራዊ ጥናት Science/Social Studies | | ሳይንስ/ማህበራዊ ጥናት Science/Social Studies |
| | ጣልቃ ገብ ድጋፎች_ Intervention Supports<br>የማህበራዊ ስሜታዊ ደህንነት<br>ማህበረሰባዊ ክበቦች<br>ክህሎት በትኩረት እንዲንሠራራ ማድረግ | | ጣልቃ ገብ ድጋፎች_ Intervention Supports<br>የማህበራዊ ስሜታዊ ደህንነት<br>ማህበረሰባዊ ክበቦች<br>ክህሎት በትኩረት እንዲንሠራራ ማድረግ |
| | ከትምህርት ቤት የሚሰናበቱበት ሠዓት | | ከትምህርት ቤት የሚሰናበቱበት ሠዓት |
| | ቡድን B እቤት _ በቨርቹወል ትምህርት | | ቡድን A እቤት _ በቨርቹወል ትምህርት |

* የ ESOLአገልግሎቶች ቀኑን ሙሉ እንደሚካሄዱ የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል
* ቀኑን ሙሉ የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች እንደሚኖሩ የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል
* ናሙና መርሃግብር – የክፍለጊዜዎቹ ርዝመት፣ የሚጀመርበት እና የሚያበቃበት ጊዜ ሊለወጥ ይችላል

# የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅይጥ የቨርቹወል ትምህርት ናሙና መርሃግብር

| | ሰኞ (ቡድን A) | ማክሰኞ (ቡድን A) | ረቡዕ | ሐሙስ (ቡድን B) | ዓርብ (ቡድን B) |
|---|---|---|---|---|---|
| A.M. | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 1** (85 ደቂቃ) | | ለተማሪዎች ሳይነካኩና ሳይጠጋጉ መማር እና የተናጠል ሥራ የተናጠል እና የትብብር እቅድ ስለ ማርክ አሠጣጥ ሙያዊ እድገት በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 1** (85 ደቂቃ) | |
| A.M. | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 2** (85 ደቂቃ) | | | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 2** (85 ደቂቃ) | |
| A.M. | **3ኛ ክፍለጊዜ Period 3** (120 ደቂቃ፣ በዚህ ክፍል 35 ደቂቃ የምሣ ጊዜን ጨምሮ) | | | **3ኛ ክፍለጊዜ Period 3** (120 ደቂቃ፣ በዚህ ክፍል 35 ደቂቃ የምሣ ጊዜን ጨምሮ) | |
| ከሠዓት በኋላ- **P.M.** | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 4** (85 ደቂቃ) | | | **4ኛ ክፍለጊዜ-Period 4** (85 ደቂቃ) | |
| A.M. | | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ_ **Period 6** (85 ደቂቃ) | | | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 6** (85 ደቂቃ) |
| A.M. | | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 7** (85 ደቂቃ) | | | የመጀመሪያ ክፍለጊዜ- **Period 7** (85 ደቂቃ) |
| ከሠዓት በኋላ- **P.M.** | | **8ኛ ክፍለጊዜ-Period 8** (120 ደቂቃ፣ በዚህ ክፍል 35 ደቂቃ የምሣ ጊዜን ይጨምራል) | | | **8ኛ ክፍለጊዜ-Period 8** (120 ደቂቃ፣ በዚህ ክፍል 35 ደቂቃ የምሣ ጊዜን ይጨምራል) |
| ከሠዓት በኋላ- **P.M.** | | ***Support/Homeroom*** (85 ደቂቃ) | | | ***Support/Homeroom*** (85 ደቂቃ) |

* የ ESOL አገልግሎቶች ቀኑን ሙሉ እንደሚካሄዱ የጊዜ ሠሌዳ ይደረጋል
* ቀኑን ሙሉ የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች የሚካሄዱበት የጊዜ ሠሌዳ ይሆናል
* ናሙና መርሃግብር – የክፍለጊዜዎቹ ርዝመት፣ እና የሚጀመርበት እና የሚያበቃበት ጊዜ ሊለወጥ ይችላል
* ማሳሰቢያ፡- የ A/B ቡድን ፈረቃ፣ በእሮብ ቀን የቀጥታ ስርጭት ትምህርት አይኖርም
* ማሳሰቢያ፡- የ A/B ፈረቃዎች ቡድን የሚኖረው ለአንደኛ ደረጃ (ኤለመንተሪ) እና ለመካከለኛ ደረጃ ብቻ ነው

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅይጥ የቨርቹዋል ትምህርት ናሙና መርሃግብር

| 1ኛ ሣምንት | Group A | Group B | Group C |
|---|---|---|---|
| ሰኞ | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ በአካል Periods 1 - 4 in person | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home |
| ማክሰኞ | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ በአካል Periods 1 - 4 in person | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home |
| እሮብ | **የተማሪ/መምህር ተግባር እና የሚጀመርበት ቀን**<br>• የተማሪዎች ሳይነካኩና ሳይጠጋጉ መማር እና የተናጠል ሥራ<br>• ለሠራተኞች የተናጠል እና በትብብር የመሥራት እቅድ<br>• ስለ ማርክ አሠጣጥ<br>• የሙያ እድገት<br>• በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ | | |
| ሀሙስ | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ በአካል Periods 1 - 4 in person |
| አርብ | ከ 6 እስከ 8 ክፍለጊዜ በአካል *በተጨማሪ የክፍል ትምህርት ድጋፍ ክፍለጊዜ* | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home |

| 2ኛ ሣምንት | Group A | Group B | Group C |
|---|---|---|---|
| ሰኞ | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከ 6 እስከ 8 ክፍለጊዜ በአካል *በተጨማሪ የክፍል ትምህርት ድጋፍ ክፍለጊዜ* | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home |
| ማክሰኞ | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከ 6 እስከ 8 ክፍለጊዜ በአካል *በተጨማሪ የክፍል ትምህርት ድጋፍ ክፍለጊዜ* |
| እሮብ | **የተማሪ/መምህር ተግባር እና የሚጀመርበት ቀን**<br>• የተማሪዎች ሳይነካኩና ሳይጠጋጉ መማር እና የተናጠል ሥራ<br>• ለሠራተኞች የተናጠል እና በትብብር የመሥራት እቅድ<br>• ስለ ማርክ አሠጣጥ<br>• የሙያ እድገት<br>• በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ | | |
| ሀሙስ | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ በአካል Periods 1 - 4 in person | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home |
| አርብ | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ በአካል Periods 1 - 4 in person | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home |

* የ ESOL አገልግሎቶች ቀድሞውኑ የሚካሄዱበት የጊዜ ሠሌዳ ይቀጥላል
* ቀኑን ሙሉ የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች እንደሚኖሩ የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል
* ናሙና መርሃግብር — የክፍለጊዜዎች ርዝመት፣ እና የሚጀመርበት እና የሚያበቃበት ጊዜ ሊለወጥ ይችላል

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅይጥ የቨርቹወል ትምህርት ናሙና መርሃግብር (የቀጠለ)

| 3ኛ ሣምንት | Group A | Group B | Group C |
|---|---|---|---|
| ሰኞ | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ በአካል Periods 1 - 4 in person |
| ማክሰኞ | ከ 6 እስከ 8 ክፍለጊዜ በአካል *በተጨማሪ የክፍል ትምህርት ድጋፍ ክፍለጊዜ* | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home |
| እሮብ | **የተማሪ/መምህር ተግባር እና የሚጀመርበት ቀን**<br>• የተማሪዎች ሳይነካኩና ሳይጠጋጉ መማር እና የተናጠል ሥራ<br>• ለሠራተኞች የተናጠል እና በትብብር የመሥራት እቅድ<br>• ስለ ማርክ አሠጣጥ<br>• የሙያ እድገት<br>• በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ | | |
| ሀሙስ | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከ 6 እስከ 8 ክፍለጊዜ በአካል *በተጨማሪ የክፍል ትምህርት ድጋፍ የሚሰጥበት ክፍለጊዜ* | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home |
| አርብ | ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 6 - 8 at home | ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ እቤት ውስጥ Periods 1 - 4 at home | ከ 6 እስከ 8 ክፍለጊዜ በአካል *በተጨማሪ የክፍል ትምህርት ድጋፍ ክፍለጊዜ* |

* የ ESOL አገልግሎቶች ቀኑን ሙሉ እንደሚካሄዱ የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል
* ቀኑን ሙሉ የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች እንደሚኖሩ የጊዜ ሠሌዳ ይዘጋጃል
* ናሙና መርሃግብር – የክፍለጊዜዎቹ ርዝመት፣ የሚጀመርበት እና የሚያበቃበት ጊዜ ሊለወጥ ይችላል

# በቨርቹወል ብቻ የትምህርት—ሞዴል 2

## ቨርቹወል ትምህርት-Virtual Learning

የትምህርት ዓመት በሚጀመርበት ጊዜ በአካል ተገኝቶ የመማር ፍላጎት ለሌላቸው ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አጠቃላይ የቨርቹወል ትምህርት የመስጠት "comprehensive virtual learning opportunities" እድሎችን ይሰጣል።

## አብዛኛውን በመምህር የሚካሄድ/የሚመራ ትምህርት

ቨርቹወል ትምህርት አብዛኛውን በቀጥታ ስርጭት፣ በአስተማሪ -እየተመራ ትምህርት ይሰጣል።

## አንዳንድ በተናጠል የሚካሄዱ ትምህርቶች

የቨርቹወል ትምህርት የተወሰኑ የብቻ (የተናጠል) ትምህርቶችን ይጨምራል። ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው በይበልጥ በሚያመቻቸው ጊዜ ትምህርት የመከታተል አማራጭ ይኖርቻዋል።፡

*የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እየጨመረ ከሄደና እንዲዘጋ ሁኔታው የሚያስገድድ ከሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በስቴት እና/ወይም በአካባቢ ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ሁሉንም ተማሪዎች ወደ ቨርቹወል ትምህርት ብቻ ለመመለስ ይዘጋጃል።

# ናሙና መርሃግብር -**Sample** Schedules

## የኤለመንተሪ ቨርቹወል ትምህርት ብቻ ናሙና መርሃግብር

<table>
<tr><th>ሰዓት</th><th>ሰኞ እና ማክሰኞ</th><th>ረቡዕ</th><th>ሃሙስ እና አርብ</th></tr>
<tr><td rowspan="4">A.M.</td><td>የክፍል ተማሪዎች ስብሰባ</td><td rowspan="7">• የተማሪ የተናጠል ትምህርት- Asynchronous Learning<br>• በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ<br>• የተናጠል እና የትብብር እቅድ<br>• ስለ ማርክ አሠጣጥ<br>• ሙያዊ እድገት</td><td>የክፍል ተማሪዎች ስብሰባ</td></tr>
<tr><td>የሂሳብ ትምህርት</td><td>የሂሳብ ትምህርት</td></tr>
<tr><td>እንግሊዝኛ/የቋንቋ ኪነጥበባት</td><td>እንግሊዝኛ/የቋንቋ ኪነጥበባት</td></tr>
<tr><td>ምሳ</td><td>ምሳ</td></tr>
<tr><td rowspan="3">ከሠዓት በኋላ- P.M.</td><td>የማህበራዊ ስሜታዊነት ትምህርቶች፣ አነስተኛ ቡድኖች፣ ጣልቃመግባትና ወይም ድጋፎችን መስጠት</td><td>የማህበራዊ ስሜታዊነት ትምህርቶች፣ አነስተኛ ቡድኖች፣ ጣልቃመግባትና ወይም ድጋፎችን መስጠት</td></tr>
<tr><td>ሳይንስ ወይም ማህበራዊ ጥናት Science or Social Studies</td><td>ሳይንስ ወይም ማህበራዊ ጥናት Science or Social Studies</td></tr>
<tr><td>ስነጥበብ፣ ሙዚቃ ወይም የአካል ማጎልመሻ ትምህርት Art, Music or P.E.</td><td>ስነጥበብ፣ ሙዚቃ ወይም የአካል ማጎልመሻ ትምህርት Art, Music or P.E.</td></tr>
</table>

* ተማሪዎች በከፊል የትምህርት መስጫ ክፍለጊዜዎች በቀጥታ ስርጭት ትምህርት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድን ትምህርት፣ የውይይት ቡድኖች እና በተናጠል ለየብቻቸው በሚሰጡ ትምህርቶች ላይ ይሰማራሉ።
* ይሄ የናሙና መርሃግብር ብቻ ነው። ሠዓቶቹ እና የክፍል ቅደምተከተል እንደየትምህርት ቤቱ ደረጃ ይስተካከላል።
* ESOL እና የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች በጊዜ ሠሌዳው ቀኑን ሙሉ ይካሄዳል።

# የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቨርቹወል ብቻ የናሙና መርሃግብር

| ሰኞ | ማክሰኞ | ሮብ | ሀሙስ | አርብ |
|---|---|---|---|---|
| **ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ Periods 1 - 4** | **ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ Periods 5 - 8 (5ኛው ክፍለጊዜ የምሣ ሠዓት ነው)** | • የተማሪ የተናጠል ትምህርት- Asynchronous Learning<br>• በተናጠል ግላዊ የተማሪ ድጋፍ<br>• የተናጠል እና የትብብር እቅድ<br>• ስለ ማርክ አሠጣጥ<br>• የሙያ እድገት | **ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍለጊዜ Periods 1 - 4** | **ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍለጊዜ Periods 5 - 8 (5ኛው ክፍለጊዜ የምሣ ሠዓት ነው)** |
| A.M. *አንደኛ ክፍለጊዜ-Period 1* | A.M. *ስድስተኛ ክፍለጊዜ-Period 6* | | A.M. *አንደኛ ክፍለጊዜ-Period 1* | A.M. *ስድስተኛ ክፍለጊዜ-Period 6* |
| A.M. *አንደኛ ክፍለጊዜ-Period 2* | A.M. *7ኛ ክፍለጊዜ-Period 7* | | A.M. *አንደኛ ክፍለጊዜ-Period 2* | A.M. *አንደኛ ክፍለጊዜ-Period 7* |
| ምሳ | ምሳ | | ምሳ | ምሳ |
| P.M.*ሦስተኛ ክፍለጊዜ-Period 3* | P.M.*ስምንተኛ ክፍለጊዜ-Period 8* | | P.M.*ሦስተኛ ክፍለጊዜ-Period 3* | P.M.*ስምንተኛ ክፍለጊዜ-Period 8* |
| P.M.*ስምንተኛ ክፍለጊዜ-Period 4* | ከሠዓት በኋላ-P.M. *Homeroom* | | ከሠዓት በኋላ-P.M. *4ኛ ክፍለጊዜ Period 4* | P.M.*Homeroom/Support Period* |

* ተማሪዎች በክፈል የትምህርት መስጫ ክፍለጊዜዎች የቀጥታ ትምህርት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድን ትምህርት፣ የውይይት ቡድኖች እና በተናጠል ለየብቻቸው በሚሰጡ ትምህርቶች ላይ ይሰማራሉ።

* ይሄ የናሙና መርሃግብር ብቻ ነው። ሠዓቶቹ እና የክፍል ቅደምተከተል እንደየትምህርት ቤቱ ደረጃ ይስተካከላል።

* ESOL እና የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች የሙሉ ቀን የጊዜ ሠሌዳ ይኖራቸዋል።


# የትግበራ - እሳቤዎች Operational - Considerations

ረቂቅ መመሪያ

## ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ወደ ቤታቸው በሠላም ማጓጓዝ

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአጠቃላይ ትምህርት ማጓጓዣ አውቶቡስ የተሳፋሪዎች ቁጥር በወቅቱ ባለው የጤና መመሪያ መሠረት 12 ተሳፋሪዎች ብቻ እንዲሆኑ ይገድባል።
- የአቅም ውስንነት ካላቸው፣ ቤተሰቦች የትምህርት ቤት አውቶቡስ ማጓጓዣ የመጠየቅ አማራጭ ይኖራቸዋል፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ለመምጣት የትምህርት ቤት አውቶቡስ የሚፈልጉ ተማሪዎችን ለማጓጓዝ የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን፣ በህዝብ ጤንነት መመሪያ ምክንያት የማጓጓዝ አቅም ውስንነት አለብን። ባሉት የትምህርት ቤት አውቶቡሶች አቅም መጠን ለኤለመንተሪ እና ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡
- ስለኮቪድ-19 መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ እንዲያጤኑ እና የአውቶቡስ ንጽህና አጠባበቅን ጭምር በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ለሠራተኞች ስልጠናዎችን ይሰጣል።

### የአውቶቡስ መቀመጫ ብዛት



# ጠንካራ የጤንነት እና የደህንነት እሳቤዎች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ቤቶች እና በቢሮዎች በጠቅላላ የሚከተሉትን የጤንነት እና የደህንነት እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደረጋል፡፡

## ስለጤንነትመጠይቅ

ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች የጤና መጠይቆች

## የሚኖረውጥቂት/ውስንነው

ወደ ትምህርት ቤት የመግባት ሁኔታ በተቻለ መጠን ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች ብቻ የተገደበ ይሆናል።

## አካላዊርቀት

በህንሳዎች እና በመማሪያ ክፍሎች ይበልጥ ሰፊ ቦታዎች እና ጥቂት የተማሪዎች ቁጥር ብቻ ይኖራል፡፡ የክፍል ውስጥ አቀማመጥ፣ የመድረሻ እና የመልቀቂያ ሁኔታ አካላዊ ርቀትን **ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ ይሻሻላል።**

## እጅመታጠብ

ቀኑን በሙሉ እና ከምግብ በፊት እና በኋላ እጅ መታጠብ አስፈላጊ መሆኑን እናበረታታለን፡፡

## ቀጣይድጋፎች

ሲስተም አቀፍ የሆነ ውጤታማ የጤንነት እና የደህንነት ተግባሮችን በእርግጠኝነት ለማካሄድ የትምህርት ቤት መሪዎች/አስተዳዳሪዎች በተከታታይ የትግበራ ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡

## የእቃማስቀመጫቦታ

ተማሪዎች በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በቂ የእቃ ማስቀመጫ ቦታ እንዲኖራቸው ተጨማሪ የእቃ መያዣዎችን ታዘዋል።

## ፊትንመሸፈን

ፊት መሸፈኛ ስለሚያስፈልግ ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች እንደአስፈላጊነቱ ይሰጣል።

## የእጅጤንነትመጠበቂያ Hand Sanitizer

የእጅ ጤንነት መጠበቂያ Hand Sanitizer የሚሰጠው በመግቢያዎች ላይ በሚገኙ የእጅ ጤንነት መጠበቂያ ጣቢያዎች፣ በመማሪያ ክፍሎች እና በጋራ መጠቀሚያ ስፍራዎች ነው፡፡

## ስልጠና

ስለ ኮቪድ-19 መከላከል እና ማህበራዊ/አካላዊ ርቀትን ስለመጠበቅ እና ፊት ስለመሸፈን ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ምዝገባ እና ቀጣይ ግንኙነት ስልጠናውን ይበልጥ የተሟላ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የአቅርቦት ቁሳቁሶችን ከሌሎች ጋር መጋራት አይኖርም

በተለይም በኤለመንተሪ ደረጃ እርስ በርስ መጋራትን ለማስወገድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በጠቅላላ የትምህርት ቤት ግብአቶችን/ቁሳቁሶችን በተጨማሪ ያዛል፡፡

## ከሞንትጎመሪካውንቲፐብሊክስኩልስየተሰጡ የትምህርትመገልገያእቃዎች-ዲቫይሶች-MCPS Issued Devices

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Chromebooks እና ሌሎች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተለይተው ሲታወቁ መስጠት ይቀጥላል።

## ጽዳት-ንጽህና

የ MCPS ትምህርት ቤቶች፣ ፋሲሊቲዎች እና አውቶቡሶች በጠቅላላ የዘወትር ጽዳት ይደረጋል።

# የምግብ አገልግሎቶች

### ምሣ ይዘው እንዲመጡ እናበረታታለን

ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው የራሳቸውን ምግብ ይዘው እንዲመጡ ይበረታታሉ፣ ወይም በጋራ ከሚበሉበት የምግብ አዳራሽ ወይም ካፍቴሪያ ይልቅ በመማሪያ ክፍል ውስጥ እያንዳንዳቸው በተለይ ሣህን እንዲመገቡ ይደረጋል።

### እጅ መታጠብን ተግባራዊ ማድረግ

በውኃና በሣሙና እጅ መታጠብን በጥብቅ ተግባራዊ እናደርጋለን ምግብ **ከተበላ በኋላ።**

### የመጠበቂያ ቦታዎችን ከብክለት ማጥራት

ሁልጊዜ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎችን ንጽህና እንጠብቃለን።

### ምግብ መጋራት አይፈቀድም

በተማሪዎች መካከል ምግብ እንዳይጋሩ “do not share” የሚለውን መርህ ተግባራዊ ማድረግ እንቀጥላለን።

### የምግብ አለርጂ እቅዶችን መገምገም

ትምህርት ቤት ከመጀመሩ አስቀድሞ፣ አስተማሪዎች እና የትምህርት ቤት ሃላፊዎች የምግብ አለርጂ ያለባቸውን ተማሪዎች በጠቅላላ ስለምግብ አለርጂ እና 504 plans እቅዶችን ይገመግማሉ፡፡

# የማንሠራራት-የማገገም እቅድ መርሃግብር

**የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ**
ጁን 2020

**የወላጆች እና የሠራተኞች የዳሰሳ ጥናት**
ጁን 2020

**ለትምህርት ቦርድ የሚቀርብበት ጊዜ**
ጁላይ 14/2020

**ለሠራተኞች ስለ ፎል የመንሠራራት-የማገገም መጠይቆች**
ጁላይ 18 – ጁላይ 26/2020

**ለቤተሰብ የምዝገባ ክፍለጊዜ**
ከጁላይ 27 - ኦገስት 7/2020

**ስለ ማንሠራራት-ማገገሚያ ማጠቃለያ እቅድ ለ MSDE ይቀርባል**
ኦገስት 2020 የመጀመሪያዎቹ ቀናት

**ትምህርት ቤት የሚጀመርበት ቀን**
ኦገስት 31/2020

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች



## የእኔን ልጅ ጤንነትና ደህንነት በህንፃዎቻችሁ ውስጥ እንዴት ትጠብቃላችሁ?

ስለ 2020-2021 የትምህርት ዓመት ያደረግነው ውይይት እና ዝግጅት መሠረት ያደረገው ጤና እና ደህንነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ይኼውም ተማሪዎቻችንን፣ የትምህርት ባለሙያዎቻን፣ አስተዳዳሪዎችን እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ወደ ህንፃዎቻችን እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ቅድሚያ ትኩረት ሰጥተን በምናደርጋቸው ዝግጅቶች ዙርያ ያውጠነጠነ ነው። በዚህ ወቅት አዲስ በተከሰተው የጤና እና የደህንነት ጥበቃ ማእቀፎች ውስጥ ሆነን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ከተለመደው አይነት የተለየ ቢመስልም፣ ተማሪዎቻችን በሙሉ ሠላም፣ ጤንነት፣ እና ደህንነት ተሰምቷቸው በደስታ የሚማሩበት ምህዳር እንደሚኖራቸው እንደቀድሞው የፀና ቁርጠኝነት አለን። ስለ ሠራተኞቻችን እና ቤተሰቦች የጤንነት ፍላጎታቸውን በአንክሮ የምንመለከት ከመሆኑም በላይ ወደ ህንፃዎቻችን መመለስ ለማይፈልጉት አማራጭ እንሰጣለን።

የጤና እና ደህንነት እርምጃዎችን በተመለከተ የተዋሱን-የቫይረሱን ስርጭት ስጋት ለመቀነስ የእጅ ንጽህና መጠበቂያ-hand sanitizer መጠቀም እና እጅ መታጠብን፣ ፊት መሸፈንን፣ እና አካላዊ ርቀት መጠበቅን ትኩረት እንሰጣለን።

## በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ቢፈጠር ምን ይደረጋል? እንዴት ወይም ለምን የመማሪያ ክፍልን ወይም ትምህርት ቤትን ለመዝጋት ትወስናላችሁ?

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እየጨመረ እንዲዘጋ ሁኔታው የሚያስገድድ ከሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በስቴት እና/ወይም በአካባቢ ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ሁሉንም ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ቨርቹወል ትምህርት እቅድ ለመመለስ ይዘጋጃል።

## በተማሪዎች መካከል ጭምብል-ማስክ እንዲለብሱ እንዴት ተግባራዊ ታደርጋላችሁ?

አዋቂዎች-ጎልማሶች እና ተማሪዎች በሙሉ ጭምብል-ማስክ እንዲለብሱ ይደረጋል-ይታዘዛሉ።

## የእኔ ልጅ በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ እንዲሆን-እንድትሆን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሃሳቤን እንዴት ለመግለጽ እችላለሁ?

በምዝገባ ወቅት ቤተሰቦች የሚፈልጉትን የትምህርት አሠጣጥ ሞዴል ለመምረጥ ይችላሉ። የመረጡት ሞዴል ለሴሚስተሩ በጠቅላላ የሚሆን ነው። ነገር ግን፣ ቤተሰብ ምጫቸውን ለመቀየር ከፈለጉ፣ የአሠራር ሒደት ይኖራል።

* **ስለ ፎል የመንሠራሪያ-ማገገሚያ እቅድ የሚነሱ በርካታ ጥያቄዎች-extensive FAQs በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ-ገጽ ላይ ይወጣሉ።**

# ግብረመልስ **አቅርብ - Submit** Feedback

SCAN ME

## ግብረመልስ

የእርስዎን ግብረመልስ በ MCPS የፎል 2020 ማገገሚያ ረቂቅ እቅድ ላይ ያቅርቡ። የእርስዎ ግብረመልስ ስለ እቅዳችን መረጃ ለማግኘት አስፈላጊ ይሆናል።

ምክረሃሳብ-ግብረመልስ ለመስጠት
ወደዚህ ድረ-ገጽ ይሂዱ
www.MCPSSubmitFeedback.org

